# ለጉዞዎች የወላጅ/ሞግዚት ፈቃድ መስጫ (MCPS መጓጓዣ አያቀርብም)

የት/ቤት ድጋፍ እና የመሻሻል ፅ/ቤት
ሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850

MCPS ቅጽ 560-31
ሀምሌ 2018

## ክፍል I :- በጉዞ አቀናባሪ/ስፖንሰር የሚሞላ።

ት/ቤት ______________________ ክፍልደረጃ/ቡድን ______________________

የጉዞ ቀን (ቀኖች) ______________________ ከ ______a.m./p.m. እስከ ______a.m./p.m. የተማሪ ወጪ/ዋጋ ______

የጉዞ ቦታ (ከተማንና ስቴትን አካትቱ) ______________________

የትራንስፖርት ዝግጅት:-
☐ MCPS ያፀደቀው አውቶቡስ የማጓጓዣ ድርጅት (ስም ______________________ )
☐ የህዝብ መጓጓዣ/ትራንስፖርቴሽን (ይገለጽ ______________________ ) ☐ የእግር ጉዞ
☐ ከ ጋር በመኪና ይሄዳል/ትሄዳለች ☐ ወላጅ ☐ ሞግዚት ☐ ሠራተኛ ☐ ተማሪ

የጉዞ ዓላማ ______________________

አቀናባሪ/ስፖንሰር የት/ቤት ባልደረባ______________________ ቀን ______/______/______

ስሙ/ሟ ከዚህ በታች የሚገኘው ተማሪ እላይ በተጠቀሰው እንቅስቃሴ ላለመሳተፍ ሊፈቀድለ(ላ)ት ይችላል።

የርእሰ መምህር ፊርማ ______________________ ቀን ______/______/______

## ክፍል II:- በወላጅ/ሞግዚት፣ ወይም እድሜ የሚፈቅድለ(ላ)ት ተማሪ የሚሞላ

A. ፋይናንስ/ገንዘብ/ ክፍያን በተመለከተ የወላጅ/የሞግዚት ኃላፊነት
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመስክ ጉዞዎች የፋይናንስ ክፍያ ሀላፊነት እንዳለብዎት እንዲያውቁ ይፈልጋል።

ዋጋ:-— እንደጉዞው አይነት/ሁኔታ፣ዋጋው የመጓጓዣ፣ የቲኬት ወይም መግቢያ ዋጋ፣ ምግብ፣ ሆቴል፣ እና/ወይም የጉዞ ወኪል አገልግሎት ዋጋ ሊያካትት ይችላል።

ክፍያ - በቼክ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ ወይም የሚቻል ከሆነ በአውታረ መረብ ለት/ቤት ክፍያ መፈጸም ይቻላል። ነገር ግን፣ ጥሬ ገንዘብ በልጅዎ አስይዘው ወደ ት/ቤት እንዳይልኩ ይመከራሉ። በሆነ ምክንያት በባንክ የተመለሰ ቼክ የ$25.00 የተመላሽ ቼክ ቅጣት ያስከትላል። አማራጭ የአከፋፈል ዘዴ ለማድረግ እባክዎን የት/ቤቱን አማካሪ/ካውንስለር ወይም የት/ቤቱን አስተዳዳሪ ያግኙ። የመስክ ጉዞው ዋጋ በቤተሰብዎ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ስኮላርሺፖች፣ቅናሽ ዋጋ፣ ወይም የተሻሻለ የአከፋፈል መርሃግብሮች አሉ።

መዘግየት፣ ለውጥ፣ ወይም ጉዞ መሠረዝ:- አንዳንድ ጊዜ ጉዞን ማሸጋገር፣ መቀየር፣ ወይም በመጥፎ አየር ምክንያት፣ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ቢኖሩ ለደህንነት ሲባል ጉዞ መሠረዝ አስፈላጊ ነዉ። አንዳንድ ጊዜ፣ አንድ ጉዞ ሲሰረዝ፣ ሲለወጥ ወይም ሲዘገይ፣ የቅድሚያ ክፍያና የመሰረዝ ክፍያዎች ወይም ሌሎች ክፍያዎች ለMCPS ሊመለሱ አይችሉም። ለምሳሌ፣ የመጓጓዣ ምዝገባዎች፣ የተገዙ ቲኬቶች፣ ወይም ለጉዞ ወኪል የተከናወኑ ክፍያዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ሁልጊዜ ገንዘብ ተመላሽ ማድረግ አይቻልም፣ ቢሆንም እርስዎ የከፈሉትን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመመለስ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

ተጨማሪ ክፍያ/ወጪ:- ጉዞ የሚዘገይ ከሆነ፣ ከተስተጓጎለ፣ ወይም ጉዞ ከተጀመረ በኋላ የተቀየረ እንደሆነና ለደህንነት ወይም ለሌሎች ምክንያቶች ተብሎ ተማሪዎች ከታሰበው ጊዜ በላይ ከቤታቸው እና ከት/ቤታቸው ርቀው የመቆየት ሁኔታ ካጋጠመ ለምግብ፣ ለመጠለያ፣ እና ለተጨማሪ ወይም አማራጭ ማጓጓዣ/ትራንስፖርቴሽን የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ክፍያዎች ሊኖር ይችላል። ይህ ከሆነ፣ ተጨማሪ ወጭዎችን ዝቅ ለማድረግ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን፣ ቢሆንም እነዚህን ተጨማሪ ወጭዎች ለልጅዎ/ልጆችዎ የመክፈል ሀላፊነት አለብዎት።

B. በኃኪም ትዕዛዝ የሚወሰድ መድሃኒት
የግዴታ አስፈላጊ ከሆነ፣ በትምህርት ቀን እና የምሽት አዳር የመስክ ጉዞ ሲኖር ወላጅ/ሞግዚት ለተማሪዎች የት/ቤት ሠራተኞች መድኃኒት ለመስጠት እንዲችሉ MCPS ቅጽ 525-13 በኃኪም የታዘዘ መድኃኒት የመስጠት ፈቃድ፣ ከተጠያቂነት ነፃ የሚያደርግ ስምምነት እና/ወይም MCPS ቅጽ 525-14 በድንገተኛ ሁኔታ Anaphylaxis በሽታ ላለበ(ባ)ት ተማሪ Epinephrine Auto-Injector ለመጠቀም የሚያስችል ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርግ ስምምነት ከላይ የተጠቀሱት ቅጾች የተፈረሙ ከሆነ ይስጣሉ።

☐ ልጄ በመስክ ጉዞ ላይ ሲሳተፍ/ስትሳተፍ መድኃኒት መውሰድ አለበ(ባ)ት። MCPS ቅጽ 525-13 እና/ወይም MCPS ቅጽ 525-14 ተሞልቶ (የመስክ ጉዞ ከመሆኑ ቢያንስ አንድ ሳምንት አስቀድሞ) እና በልጄ ት/ቤት የጤና ክፍል ፋይል ላይ ይገኛል። ማሳሰቢያ:- በሃኪም የታዘዙ መድኃኒቶች በፋርማሲስት አማካይነት በትክክል የታሸጉና/የመድኃኒት ሌብሉ/አወሳሰዱ እና ፈቃድ ያለው መድኃኒት የሚያዘው የተጣጣመ መሆን አለበት፣ ከመደርደሪያ ላይ የሚገዙ መድሃኒቶች በኦርጅናል የመድኃኒት መያዣ ሆኖ ስለ መድሃኒቱ አወሳሰድ መግለጫ እና የጥንቃቄ ሁኔታ የሚገልጽ ሌብል ከአምራቹ ኖሮት የታሸገ መሆን አለበት። ለተጨማሪ ዝርዝር ቅጽ 525-13 እና/ወይም 525-14 ይመልከቱ።

C. የጉዞ ኢንሹራንስን የሚመለከት ኢንፎርሜሽን/መረጃ
ጉዞ ከተሰረዘ፣ ከዘገየ፣ ወይም የሚደናቀፍ ከሆነ፣ ወይም በህመም እና በመሣሠሉት ምክንያት ልጁ/ልጅቷ ጉዞው ላይ ለመሳተፍ የማይችል/የማትችል ከሆነ የጉዞ ኢንሹራንስ ወጪ በመሸፈን ይረዳ ይሆናል። የጉዞ ዋስትና ዋጋ እንደ ኩባንያውና እንደመረጡት የዋስትና ፕላን ሊለያይ ይችላል። የሆነ ሆኖ፣ ይጠንቀቁ፣ በጥንቃቄ ምክንያት በት/ቤቱ የተሰረዘን ጉዞ የጉዞ መድህን ኩባንያዎች አይሸፍኑም። ት/ቤት ለቡድን ዋስትና ተደራድሮ የመስክ ጉዞው ዋጋ ላይ ካላካተተው በስተቀር፣ የጉዞ ዋስትና የመግዛት ጥያቄ ውሳኔው የርስዎ ፋንታ ነው። የጉዞ ዋስትና ለመግዛት ከወሰኑ፣ እርስዎ አቀናጅተዉ ወጪዉንም መክፈል አለብዎት።

የተማሪ ስም ______________________ መምህር ______________________

☐ ልጄ እላይ በተገለፀው እንቅስቃሴ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ፈቅጃለሁ።

☐ ልጄ እላይ በተገለፀው እንቅስቃሴ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ አልፈቅድም።

☐ በዚህ የመስክ ጉዞ አጃቢነት ፈቃደኛ ለመሆን እፈልጋለሁ።*
*እባክዎ ይገንዘቡ በጎ ፈቃደኞች በሙሉ በድረገጽ የሚወሰደውን ስልጠና ስለ ልጆች ጥቃት መከላከል፣ ማጤን፣ እና የልጆችን ጉስቁልና እና ችላ ተብለው ከሆነ ሪፖርት ማድረግን ማጠናቀቅ አለባቸው። ለተራዘመ የመስክ ጉዞ ቀን (7:00 p.m በኋላ ለመመለስ) እና ለምሽት አዳር የመስክ ጉዞዎች በጎ ፈቃደኞች የጣት አሻራና የበፊት የኋላ ታሪክ ማጣራት መፈጸም አለባቸው።

ወላጅ/ሞግዚት ስም ______________________ የስልክ ቁጥር ______________________

በድንገተኛ ጊዜ መገኘት የሚችል ሰው______________________ስልክ ቁጥር______________________

ወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ______________________ቀን______/______/______